# ችግራችንን ለመፍታት ወይስ ይበልጥ ለማወሳሰብ?

(ከሔኖክ ሄደቶ henhed77@yahoo.com)

ጥር 15 ቀን 2002 ዓ.ም በታተመ አውራምባ ታይምስ ጋዜጣ ላይ በአሜሪካ የሚኖሩ ሁለት ፕሮፌሰሮች ፕ/ር መሳይ ከበደ እና ፕ/ር ዓለማየሁ ገ/ማርያም በተለያዩ ርዕሶች የፃፏቸውን ጽፎች በጥሞና አነበብኩ፡፡ አንዳንዱ ሃሳብ አስገረመኝ አንዱ ደግሞ አስደነገጠኝ፡፡ የፕ/ር መሳይ ከበደ ጽሑፍ “የማንነት ፓለቲካ በአሁኗ ኢትዩጵያ” በሚል እርእስ የቀረበ ሲሆን የፕ/ር ዓለማየሁ ገ/ማርያም ጽሑፍ ደግሞ “የኢትዩጵያን ፓለቲካ ዳግም የመፍጠር አስፈላጊነት” በሚል እርእስ የቀረበ ነው፡፡ የፕ/ር መሳይ ጽሁፍ ጃዋር ሲራጅ የተባለ ደራሲ ስለ ትግራይ ብሔርተኝነት የፃፉትን ጽሁፍ መነሻ በማድረግ አስተያየታቸውን ለማቅረብ ቢሆንም በሌሎች ጽሁፎቻቸው ደጋግመው ካንፀባረቋቸው ሀሳቦች በይዘት ያልተለዩ ግንዛቤዎች አንሸራሽረዋል፡፡ በዚህ ጽሁፋቸው ፕ/ር መሳይ ካነሷቸው ጉዳዬች ጋር በቀጥታ የሚያያዝ አንድ ሀሳብ በፕ/ር አለማየሁ ጽሁፍ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይበልጥ ያስደነገጠኝ በፕ/ር አለማየሁ ጽሁፍ ውስጥ ያገኘሁት ይህ ሀሳብ ነው፡፡ የሁለቱም ፕሮፌሰሮች ጽሁፎች በአንድ አቅጣጫ አይቼ በዚህ መልክ ለመከራከር የፈለኩበትን ምክንያት ለአንባቢ ማስረዳቱ ብዙም ጠቃሚ አይደለም፡፡ ነገር ግን ክርክሬ የሀሳቦቹን ይዘት ተመሳሳይነትና መነሻዬን በበቂ ሁኔታ ማስረዳቱ አይቀርም፡፡ ስለዚህ በቀጥታ ወደ ሀሳቦቻቸው ላምራ፡፡

ፕ/ር መሳይ በኢትዮጵያ ብሔር ተኮር የሆነ የማንነት ፖለቲካ የአንቀሳቃሽነት ጉልበቱን (Mobilization power) እያጣ መሆኑን በማስመልከት ለጊዜው በማላስታውሰው አንድ “አዲስ ነገር” ጋዜጣ እትም ላይ የፃፉትን ማንበቤን አስታውሳለሁ፡፡ በወቅቱ በአሁኗ ኢትዩጲያ የማንነት ፓለቲካ (identity politics) ከፖለቲካ ሀይሎች አሰላለፍ በላይ የሆነ እውነታ መሆኑን አለማየታቸው አስገርሞኝ ነበር፡፡ በዚህ ጽሁፋቸውም ጀዋር “እንደ ኢትዮጵያ ባለች አገር በማንነት ፖለቲካ ላይ የሚሳተፉበት ወይም ይህንን ማካሄድ የሚቀጥሉበት በግልፅ አይታየኝም” ብለዋል፡፡ ጃዋር ከነ አቶ መለስ ተቃራኒ ከሆነ የትግራይ ብሄርተኝነት አስተሳሰብ በመነሳት በነ አቶ መለስ ላይ ያቀረቡትን ትንተና ፕ/ር መሳይ ተቀብለውታል፡፡

ለፕ/ር መሳይ አንድ ትግሬ ከነ አቶ መለስ ዜናዊ የትግራይ ብሄርተኝነት አስተሳሰብ በተቃራኒ መንገድም ቢሆን በማንነት ፓለቲካ ላይ መሳተፉ የማይታያቸው ከሆነ ለአንድ የኦሮሞ ተወላጅ ከነ አቶ አባዱላ ገመዳ የኦሮሞ ብሔርተኝነት አስተሳሰብ በተቃራኒ ወይም አንድ የከፋ ተወላጅ ከነ አቶ ብርሀኑ አዴሎ የከፊቾ ብሔርተኝነት በተቃራኒ መቆሙ ተገቢ ሆኖ ይታያቸው እንደሆነ ለኔ ግልጽ አይደለም፡፡ ለሁሉም ኢትዩጲያዊ ግለሰቦች በማንነት ፖለቲካ ላይ መሳተፍ የማያስፈልግ ሆኖ የሚታያቸው መሆኑንም እየገለጹ ከሆነ ቀደም ሲል ያነበብኩትን ጽሁፋቸውን በትክክል ተረድቼው ነበር ማለት ነው፡፡ ፕ/ር መሳይ በጽሁፋቸው “የብሔር ቁርጠኝነትን” ብለው በገለፁት ሀሳብ ላይ ያላቸው ተቃውሞ እኔንም ጭምር የሚጥመኝ መሆኑን እንደተጠበቀ ሆኖ በአሁኗ ኢትዮጵያ የብሔር ተኮር ፖለቲካ መሰረቶች ሰፊ መሆናቸውን መቀበል አለመፈለግ በጭራሽ ሊገባኝ የማይችል ነገር ነው፡፡

ጀዋር ይህ መደረግ የሌለበት መሆኑን ለማብራራት ፕ/ር መሳይ የሄዱበት መንገድ በጽሁፉ በትግራይ ብሔርተኝነት ላይ ከእነ አቶ መለስ አንፃር በማብራራት ያቀረበውን ምክንያት በመቀበል ነው። ፕ/ር መሳይ “በመሰረቱ ጠቅላይ ሚኒስተር መለስና ጓዶቻቸው ለምሳሌ በኢትዮጵያ በኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ስም እና ልክ ደርግ አድራጎት እንደነበረው በፀረ-ጎሰኝነት አስተዳደር መዋቅር በመታገዝ ማስተዳደር እየቻሉ ለምን በተመሳቀለ የብሔር ፖለቲካ ውስጥ ሲገቡ ቻሉ?” ብለው ጠይቀዋል። ለዚህ ጥያቄ የጀዋርን ምላሽ ካነሱ በኋላ ፕ/ር መሳይ ይህ ትርጉም ያለው የሚሆንበትን ሲያብራሩ “አቶ መለስ እና ጓዶቻቸው የተወሰነ ህዝባዊ ድጋፍ ለማግኘት ከብሔር ፖለቲካ ውጪ ምንም ምርጫ እንዳልነበራቸው ግምት ከተወሰደ ብቻ ነው” ይላሉ።

የህውሀት ታሪክ የብሔር ፖለቲካ ከተወሰነ በላይ ህዝባዊ ድጋፍ ማግኘትን የሚያስችል መሆኑን ያረጋግጣል።የዚህ ምክንያት በትግራይ ህዝብ ውስጥ ብቻ ሳይሆን እኔ በተወለድኩበት በኦሮሞ ህዝብ ውስጥም አለ። ይህን የብሔር ፓለቲካ መሰረታዊ መነሻዎች ተረድተው ጥያቄውን በመቀበል መፍትሔ መፈለግን የማይፈልጉ የፓን ኢትዩጲያ አክራሪ ብሔርተኝነት አቀንቃኞች እያወቁ “በተመቸ መርሳት” ችላ የሚሉት ነገር ነው።በመጀመሪያ የብሔር ፓለቲካን ከነ አቶ መለስ ወይም ከኢህአዴግ አስተሳሰብ አቅጣጫ ብቻ ማየት ተገቢ ነው ወይ? የኢህአዴግ አስተሳሰብ ዋነኛ መነሻ  የኢትዩጲያ ፓለቲካ ዋነኛ ቅራኔ የብሔር ጭቆና ነበር የሚል ነው። እስከማውቀው ድረስ እነ አቶ መለስን አምርረው የሚቃወሙትና ከኢህአዴግ በተመሳሳይ የሆኑት የብሔር ፓለቲካ አራማጆች እነ ዶ/ር መራራ የሚሉትም ይህንኑ ነው። እንደ እነ ዶ/ር መራራ ሁሉ በዚህ ጉዳይ ከኢህአዴግ ያልተለየ አቋም እያላቸው ኢህአዴግን የሚቃወሙ ሌሎች ወገኖችም በርካታ ናቸው። ጥያቄው ከ1960ዎቹ የለውጥ ትግል አጀንዳዎች ውስጥ ዋነኛው ሆኖ እስካሁን የዘለቀ ከመሆኑ አንጻር ሲታይ ኢህአዴግ የብሔር ፖለቲካ ወላጅ አባት ሳይሆን ልጁ ነው። የብሔር ፖለቲካ ከኢህአዴግ በላይ በሆነ መሰረት ላይ የቆመ መሆኑን ለመረዳት ሌሎች በዙ ልጆች ያሉት መሆኑ ብቻ በቂ ማረጋገጫ ነው።

ፕ/ር መሳይ በጽሁፋቸው ለሰፋ ህዝባዊ ድጋፍ ከብሔር ፓለቲካ የተሻሉ ሌሎች ምርጫዎች ያሉ መሆናቸውን እየነገሩን ከሆነ ይህ ትክክል ነው። ነገር ግን በብዙ ምክንያቶች ሕብረብሔራዊነት የተሻለ ምርጫ ቢሆንም የታሳካ ምርጫ ለመሆን አልቻለም። ባለፉት ሠላሣና ሀያ አመታት በኢትዮጵያ ከተፈጠረው የፖለቲካ ድርጅቶች በብሔር የተደራጁት እየጠነከሩ ሲታዩ በህብረ ብሔርነት የተደራጁቱ እየተዳከሙና እየተፈረካከሱ ታይተዋል። ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው? በርካታ ህብረብሔር ፓለቲካ ፓርቲዎች ውስጥ ስምና ማእረግ ካለው የብሔር ፓለቲካ ያነሰ ጎሰኝነትና ተራ ዘረኝነት ስር የሰደደ ችግር ሆኖ ለመዳከም እና ለመፍረስ ምክንያት ሲሆን ቆይቶአል። በህብረብሔር ፖለቲካ ተሳትፎ የከረረ የአገር አንድነት አቋም ያላቸው ብዙ ሰዎች በውስጣቸው ያለው ጠባብነት ምን ያህል  መራር እንደሆነ በተደጋጋሚ እድል አግኝተን፣ እኛም ሰጥተን ተመልክተናል።

ችግሩን ለማሳየት እንጂ ይህን እንደ ትልቅ ቁም ነገር ለማንሳት አይደለም። ሆኖም ትንሽ ቁምነገርም አይደለም። ለኢትዮጵያዊ ብሔርተኝነት ዋነኛው ችግር ከብሔር ተኮር ፖለቲካ የሚመነጩ ፍትሐዊ ጥያቄዎች ተለይተውና ታውቀው ምላሽ እያገኙ የአንድነት ስሜትና ፍቅር በውቀትና ጥበብ እየተገነባ አለመምጣቱ ነው። ይህንን ድክመት ከኢህአዴግ በላይ ያጠናና የሚያውቅ ያለ አይመስለኝም። የተጠናከረ ማእከላዊነትን

ለመገንባት የተደረገው ረጅም ስራ በርካታ የዳር (Peripheral) አስተሳሰብ ተገቢ ጥያቄዎችን ፈጥሮአል። የኢህአዴግ አሸናፊነት ከእነኚህ ጥያቄዎች የመነጩ አስተሳሰቦች በቆየው የማእከላዊነት አስተሳሰብ ላይ ያገኙት አሸናፊነት ውጤት ነው። የአንድነት አስተሳሰብን አሸናፊ ለማድረግ ሙሉ በሙሉ የብሔር ማንነት አስተሳሰብን ማፍረስ ትላንት በነበረው ፖለቲካ ውስጥ ብቻ የነበረ ስህተት ሳይሆን የዛሬ አገር አፍቃሪ በሆኑ ፕሮፌሰሮች አስተሳሰብ ውስጥም ያለ ስህተት ነው። ለዚህም የፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም ጽሁፍ ከፕ/ር መሳይ ሀሳብ የበለጠ ማስረጃ ነው።

ፕ/ር መሳይ "ለክፍለ ዘመናት በትግሬና በአማራ መካከል ከነበረው አንድነት አንፃር የተነጠለ የትግራይ ብሔር ማንነት ደግፎ ለመከራከር የሚያበቃ ፖለቲካዊም ሆነ ባህላዊ ማረጋጫ (ማሳመኛ) የለም" ይላሉ። በአማራና ትግራይ ሕዝቦች መካከል ለክፍለ ዘመናት የዘለቀ አንድነትና ትስስር መኖሩ ግልፅ ነው። ሰፋ አድርገን ተመሳሳይ ከሆኑ እውነታዎች ጋር ካነጻጸርን ይህ በአፋርና ሱማሌ ሕዝቦች፤ በከንባታና ሀድያ ሕዝቦች፣ በወላይታና ጋሞ ሕዝቦች መካከል ካለው የታሪክ ትስስርና አንድነት የተለየ ነው ብሎ ማሰብ ለእኔ አይታየኝም። ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔረሰቦች መካከል ለረጅም ዘመናት የዘለቀ አንድነትና ትስስር አለ ማለቱ ይቀላል። ይህ ማለት ግን በዚህ አንድነትና ትስስር ውስጥ አንዱን ከሌላው ለይቶ ለማየት የሚያስችል ፖለቲካዊ ማንነትና የባህል መገለጫዎች የሉም ማለት ነው?

በሁሉም የኢትዮጵያ ህዝቦች መካከል ባሉ ታሪካዊ ትስስሮችና አንድነት ውስጥ ልዩነት አለ። ማንም ለማየት ፈለገም አልፈለገም ይህ ልዩነት የሚታይ እውነት ነው። ይህን እውነታ አለመቀበልም ከፖለቲካ ፍላጎትና ጥቅም አንፃር አንድ ምርጫ ነው። ልዩነቱን ማወቅ እና መቀበል የአንድነት ጠንቅ ነው በሚል እሳቤ ከልዩነቱ የሚመነጩ ቅራኔዎችንና ጥያቄዎችን በአግባቡ ባለመመለስ ፕ/ር መሳይ እንደሚነግሩን ልክ ደርግ አድርጎት እንደነበረው "በፀረ-ጎሰኝነት" አስተዳደር መዋቅር በመታገዝ ማስተዳደር ይቻላል-የደርግን ስህተት ዳግም ለመስራት ከሆነ የተፈለገው። ፀረ ጎሰኝነት የምንለው ግን ምኑን ነው? በፕ/ር አለማየሁ ገ/ማርያም ጽሑፍም ውስጥ የኢትዮጵያ ፖለቲካ ዳግም ለመፍጠር ከተቀመጡት መፍትሔዎች ውስጥ አንደኛው ይህ ነው። በቀጥታ የእሳቸውን ቃል በመጠቀም ለመግለፅ "ለጋራ መጪ ጊዜ በጋራ እምነት ለተመሠረተ አዲስ ብሔራዊ ዲሞክራሳዊ ማንነት እያናዳንዱ ኢትዮጵያዊ ከብሔር ማንነቱ እንዲላቀቅ ለማንቃት ድጋፍ ማድረግም ይቻላል" ይህ እጅግ አስደንጋጭ ሀሳብ ነው። ፕ/ር ዓለማየሁ ማለት የፈለጉት ሌላ ነገር ነው ብዬ እንዳልወስድ ይህንኑ ያስቀጠሉት "ከብሔር ግንባታ ወደ ሀገር ግንባታ ሽግግር ለማድረግ አስፈላጊ የሚሆኑ አዲስ የፈጠራና ልዋጭ ሃሳቦችና..." ብለው ነው።

ይህ አዲሲቷንና ዲሞክራሳዊት ኢትዮጲያን ለመገንባት እያንዳንዱ ኢትዮጲያዊ እንደ ኦሮሞ አማራ ትግሬና ወዘተ ብቻ ማሰብ የለበትም ለማለት ከሆነ ትክክል ነው። ነገር ግን አማራነቱን፤ ትግራይነቱንና ኦሮሞነቱን ትቶ እንደኢትዮጲያዊ ብቻ ማሰብ አለበት የሚል አማረጭ ከሆነ ግን "አዲስ የፈጠራና ልዋጭ አስተሳሰብ" ሳይሆን አሮጌ፤ ያረጀና ያፈጀ አስተሳሰብ ነው። ለብሔር ማንነት ፓለቲካ መጠናከርና ለኢትዮጵያ አገራዊ ብሔርተኝነት መዳከም ምክንያት የሆነ ከታመመ ፅንስ የተወለደ ለዘመናት ሁላችንንም ተሸናፊ ያደረገን አስተሳሰብ ነው። ኢህአዴግን ለዘመናት በስልጣን ላይ እንዲቆይ የሚረዳ፤ አስተሳሰቡንም ከዚህ አንፃር ሲታይ ብዙም ስህተት የሌለበት ሆኖ እንዲታይ

የሚያደርግ “እጅ የመስጠት” መንገድ ነው፡፡ ምክንያቱም ይህ አስተሳሰብ የብሔር ፓለቲካን አስፈላጊ የሚያደርግ አክራሪ የአንድነት አስተሳሰብ ስለሆነ፡፡

እኔ የብሔር ተኮር ፓለቲካ ከሕብረ ብሔራዊነት ይልቅ ለሀገር ግንባታና አንድነት የተሻለ እድል ነው ብዬ አላምንም፡፡ የፓለቲካ ትግል ዋነኛ ግብ የሆኑ ጥቅሞች ሁሉ በስተመጨረሻ የሚመዘኑት በግለሰብ ጥቅምና እርካታ አንፃር መሆናቸው ግልፅ ነው፡፡ ይህም ሆኖ ከብዙ ግለሰቦች የጋራ መገለጫዎች የሚመነጩ መለያዎችና ፍላጎቶች ሁሉ የማያሻማ ተቀባይነት አላቸው፡፡ የማህበራዊ መብቶች መነሻ ይህ ነው፡፡ ይህን ባለመቀበል የኢትዮጵያን አንድነት ማጠናከር ይቻላል? በአገራችን ዲሞክራሲያዊ ስርዓት መገንባትስ ይቻላል?

የአገራችንን አንድነት ለማጠናከር እና የተሻለ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባት አዲስ አስተሳሰብ ሊሆን የሚገባው እያንዳንዱ ኢትዩጲያዊ የብሔር ማንነቱን ለመተው ሳይገደድ ኢትዩጲያዊ ሲሆን ወይም የብሔር ማንነቱን ለማጠናከር ኢትዩጲያዊነቱን ለመተው ሳይገደድ ነው፡፡ ነገር ግን እንደ ኢህአዴግ ለኢትዮጵዊነት የብሔር ማንነት በቅድመ ሁኔታነት ሳናቀርብ፤ እንደ ፕ/ር ዓለማየሁ አስተሳሰብ ኢትዮጵያዊ ለመሆን የብሔር ማንነትን መተውም ሳያስፈልግ በሁለቱም መካከል ግጭትና ቅራኔ ሳይኖር እያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ በየራሱ ብሔር ማንነት እየተገለጸም ኢትዮጵያዊ እንዲሆን ወይም በኢትዮጵያዊነት እየተገለፀም በኢትዮጵያዊነቱ ውስጥ በየራሱ ብሔር ማንነት መገለጽን እንደችግር እንድናይ የሚያደርግ ነገር የለም፡፡ ካለም እንዳይኖር ማድረግ ይቻላል፡፡ ትላንት ለነበረው ችግር መነሻው የብሔር ጭቆና ሆነም አልሆነ በዲሞክራሳዊ ስርአት መርህ ተፈፃሚነት ላይ በማተኮር የሁሉንም አይነት ጭቆና መሠረቶች በማስወገድ የነገይቱን ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ ማነጽ ይቻላል፡፡

በኢትዮጵያ ፖለቲካ ውስጥ በቡድን መብቶች እና በግለሰብ መብቶች ዙሪያ ያለው ክርክር ለኔ እንደሚገባኝ አንዱን ትቶ ሌላውን ለመውሰድ ሳይሆን ሁለቱንም በተሻለ ሁኔታ ለማስከበር የተሻለ መነሻ የሚሆነው የትኛው ነው የሚል ነው፡፡ የብሔር ፖለቲካን የአገር አንድነት ጠንቅ ብለን ከምናወግዝበት ደረጃ ተላልፈናል፡፡ አሁን ባለንበት ሁኔታ የተሻለ የሚሆነው ከእሱ ለሚመነጩ ተገቢ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት የአገር አንድነትን በልዩነት መነሻነት እንደገና መገንባት ነው፡፡ ለዚህ ከኢህአዴግ አስተሳሰብ የተሻሉ በርካታ አማራጮችን በማፍለቅ እና በልዩነት ላይ የቆመ አንድነት በማጠናከር የልዩነት ተቋማዊነትን ዋነኛ መጠቀሚያ ያደረገ አስተሳሰብን ማሸነፍ ይቻላል፡፡

ከዚህ ውጪ የማንነት ፖለቲካንም ሆነ የብሔር ማንነት ጥያቄን ማውገዝ ለኢትዩጵያ አንድነት ችግሮች መፍትሔ አያመጣም፡፡ በአገራችን ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመገንባትም አይጠቅመንም፡፡ በዚህ መነሻነት ሳየው የፕ/ር መሳይ ሃሳብም ሆነ የፕ/ር ዓለማየሁ ሃሳብ ችግራችንን ለመፍታት የሚረዳን ወይስ ይበልጥ የሚያወሳስብ ብዬ መጠየቅ ተገቢ መስሎ ታይቶኛል፡፡